# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band


ሐምሌ 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

## የወያኔ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ስርዓቱ ላይ እምነት እንደሌላቸው ተናገሩ፤

የዘንድሮውን የስራ ዘመን ሲፈጸም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ወደ ተመረጡበት ቦታ ወርደው ሕዝቡን እንዲያነጋግሩና እንዲያወያዩ ብሎም የህዝቡን የልብ ትርታ እንዲሰልሉ ተብሎ ወደየወረዳ ሊላኩ መሆኑ ታወቀ፡፡ወደ ወረዳዎች ለሚወርዱት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ለእያንዳንዱ አባል ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ የተደረገ መሆኑንም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዜና ገልጿል፡፡

በሁለት ወር የክረምት ጊዜ ውስጥ ከ10 ቀን ያልዘለለ የማወያየት ስራ እንዲያደርጉ ታስቦ ለእያንዳንዱ አባል 10 አስር ሺህ ብር ወጪ ተደርጎ እንዲሰጣቸው የተወሰነ ሲሆን አባሎቹ ገንዘቡ ያንሰናል በማለት ሳይወስዱ መቅረታቸውም ታውቆዋል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ በስርዓቱ ላይ እምነት እያጡ የመጡት የወያኔ ካድሬዎች አንዳችም ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ውሳኔ ሳያሳልፉ ወንበር ሲያሞቁና እጅ በማውጣት አገልግሎት ሲያበረክቱ ለአራት ዓመታት የቆዩ ሲሆን በቀጣዩ ምርጫ እንሳፈፋለን በሚል ፍርሀት የተነሳ ከአባዱላ ጋር ሙግት መግጠማቸው ታውቆዋል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎች በመዝጊያው ዕለት ወደ ተወዳደሩበት ክልል በመሄድ ከህዝቡ ጋር እንዲመክሩና የህዝቡን ስሜት እንዲሰልሉ ግዳጅ የተሰጣቸው ቢሆንም በቀጣዩ ምርጫ ላይ መወዳደራቸውና አለመወዳደራቸው ስላልተነገራቸው የተለያዩ ጥያቄ ማንሳታቸውን ምንጮቹ ተናግረዋል፡፡

ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል “ ቀጣዩ እጣ ፈንታችን ምንድነው የሚሆነው? በመጭው ምርጫ ላይ እንሳተፋለን ወይስ የስራ ዘመናችሁ አልቆዋል ተብሎ እንባረራለን? የሚሉት ጥያቄዎች እንደሚገኙበት ታውቋል።

አንድ ከደቡብ ክልል የመጣች አባል “ከወከለን ሕዝብም ሳንሆን ከፓርቲያችንም ሳንሆን እንደ ሸንኮራ ተመጥጠን ልንጣል ነው ወይ? …መቁዋቁዋሚያ ምንስ ታስቦልናል በማለት እያነባች በጠየቀችበት ወቅት አብዛኞቹ የምክር ቤት አባሎች በጭብጨባ በማጀባቸው እነ አባዱላን ግራ ያጋባ ጉዳይ እንደነበር ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በኩርፊያና በለቅሶ የተጠናቀቀው የዘንድሮው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአፈ ጉባኤው ጀምሮ እስከ ተራ አባሉ ድረስ አንገት በመድፋት የተለያዩ መሆናቸውን ከውስጥ ያገኘነው ዜና ይገልጻል፡፡

ለወያኔ ባለስልጣናት ያለው ታማኝነት እየቀነሰ የመጣው አፈ ጉባኤ ተብየው አባዱላ ገመዳ አባላቱ ቁጣ የተቀላቀለበት ንግግር ሲያደርጉ በጥሞና ከማድመጥ በስተቀር መልስ አለመስጠቱና የተፈቀደላቸው 10 ሺህ ብር ያንሰናል ብለው እምቢ በማለታቸው እርምጃ አለመውሰዱ በወያኔ ከፍተኛ

ባለስልጣናት እየተተቸ እንደሚገኝም ምንጮቹ ገልጸዋል፡፡

**የታሰሩት የፖለቲካ መሪዎች ዛሬም ፍርድ ቤት አልቀረቡም፤**

**የአረና ፓርቲው አብርሀ ደስታ ከመቀሌ ወደ ማዕከላዊ ምርመራ ገባ፤**

የህዝብ ድጋፍ የሌለውና የገዛ ካድሬዎቹ ጭምር ትችት እያቀረቡበት የሚገኘው የወያኔ ቡድን ባለፉት ሳምንታት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራር አባላትን እየመረጠ ለእስር የዳረጋቸው መሆኑ ይታወሳል።

የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሀብታሙ አያሌውና የድርጅት ጉዳይ ምክትል ኃላፊ ዳንኤል ሺበሺ የሰማያዊ ፓርቲ የብሔራዊ ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ አቶ የሺዋስ አሰፋ እንዲሁም የአረና ትግራይ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አብርሀ ደስታ እጃቸው ከተያዘበት ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በማዕከላዊ ምርመራ እስር ቤት የሚገኙ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ ፍርድ ቤት አለመቅረባቸው ታውቆዋል፡፡

አንድነት ፓርቲም ድርጊቱን በማውገዝ የታሰሩት ባስቸኳይ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ በፌዴራል ፖሊስ የማዕከላዊ ምርመራ አዛዥ እና የጸረ ሽብር ቡድኑ አዛዥ ላይ ክስ መስርቶ ሐምሌ 8 ቀን ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረገ ቢሆንም ፍርድ ቤቱም ክሱን በመዝጋት የተከሰሱትን ባለስልጣናት በነፃ አሰናብቶዋቸዋል፡፡

እስረኞቹ እስከ ዛሬ ከጠበቃ...ከቤተሰቦቻቸው...ከወዳጅ ዘመዶቻቸው እና ከሌሎችም ወገኖች ጋር እንዳይገናኙ ተከልክለው ያሉ ሲሆን ያሉበት ሁኔታ የማይታወቅ በመሆኑ ስጋት አድሮብናል በማለት ለተመሰረተው ክስ ለይስሙላ በኮታ ማሙያነት የተቀመጠው የኦህዴዱ የማዕከላዊ ምርመራ አዛዥ በችሎት ቀርቦ እንዲያስረዳ ቢደረግም ፍርድ ቤቱ ያለ አንዳች ጥያቄ በነጻ አሰናብቶታል፡፡

እስረኞቹ ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በማዕከላዊ ምርመራ እስር ቤት እንደሚገኙ የገለጸው የክሱ አቤቱታ በወንጀል ህግ ከሕገ ወጥ እስራትና አያያዝ አካልን ነፃ ማውጣት እንዲችሉ በጠበቆቻቸው አማካኝነት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ማቅረባቸው አይዘነጋም፡፡

ጠበቆቻቸው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ላይ በዝርዝር እንዳስቀመጡት ከሆነ ተከሳሽ የፌዴራል ፖሊስ የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ እስረኞቹን ሐምሌ 1 ቀን ከረፋዱ 5 ሰዓት ከመንገድ ላይ በመያዝ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው መሆኑና እጃቸው ከተያዘበት ወቅት ጀምሮ አንድም ሰው እንዳያገኙ ተደርገው እንደሚገኙ በማተት አቤቱታውን አቅርቦዋል፡፡

ጠበቆቹ አያይዘውም እስረኞቹ እስካሁን የቆዩበት ሁኔታ አደገኛ በመሆኑ የዋስትና መብታቸው ተከብሮ በውጭ ሆነው እንዲከታተሉ እንዲደረግ ጠይቀው ይሄ እንኳዋን የማይቻል ቢሆን በጠበቆቻቸው...በቤተሰቦቻቸው...በዘመዶቻቸው እንዲጎበኙ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡

ወያኔ እራሱ ባወጣው ህግ መሰረት ማንኛውም ተጠርጣሪ እጁ በተያዘ በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት የሚደነግግ ቢሆንም ሕጉን በመጣስ የያዛቸውን ሰዎች በጭለማ ክፍል አስሮ እስከ ዛሬ ያላቀረባቸው መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የአረና ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊና የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህሩ አብርሀ ደስታ  ከሌሎቹ የፖለቲካ እስረኞች በተለየ በመቀሌ ከተማ አቅራቢያ በሚገኝ እስር ቤት ውስጥ ታስሮ ሲሰቃይ የሰነበተ መሆኑና አሁን ወደ ማእከላዊ የተዛወረ መሆኑ ለፓርቲውና ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለጹ፡፡

በመቀሌ አጠገብ የሚገኘው እስር ቤት በምድር ውስጥ የተገነባና በትጥቅ ትግል ወቅት እነመለስ ከእነሱ የተለየ አቋዋም  አላቸው የተባሉትን የሚያሰቃዩበት እንደነበር ያጋለጡት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ዛሬም የሚፈሩትንና ለስልጣናቸው ያሰጋናል የሚሉዋቸውን ዜጎች በድብቅ አስረው የሚያሰቃዩበት እንደሆነ ምንጮቹ ይናገራሉ፡፡

እስር ቤቱ በመሬት ውስጥ ተቦርቡሮ የተሰራ በመሆኑ  የጸሀይ ብርሀን ጭምር ማግኘት እንደማይቻልና ብዙዎቹ ከእስር ቤቱ ሲወጡ ለዓይነ ስውርነት የሚዳረጉ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት የአረና ትግራይ አባል የሆነው አብርሀ ደስታን ከታሰረበት መቀሌ እስር ቤት አምጥተው ከሌሎቹ እስረኞች ጋር ማዕከላዊ ምርመራ እንዲገባ ያደረጉት መሆናቸው እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ተናግረዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ቡድን በሽብርተኝነት ስም አፍሶ ለ80 ቀናት በማዕከላዊ ምርመራ አስሮዋቸው የከረሙት እና ያለ አንዳች ለውጥ በፍርድ ቤት ሲንከራተቱ የነበሩት ጋዜጠኞች ጉዳይ እስረኞቹ እና የህግ ባለሙያዎች ባልተገኙበት በዝግ ችሎት ፋይሉ ተዘግቶ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲወርድ መደረጉ ታወቀ፡፡

ለወራት ሲታይበት በነበረው በአራዳ ምድብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባለፈው ቅዳሜና ሰኞ ጋዜጠኞቹና ጠበቃቻቸው ባልተገኙበት በዝግ ችሎት የፌዴራል ማዕከላዊ ምርመራ መርማሪ ፖሊሶች ባቀረቡት አቤቱታ ብቻ ግራና ቀኙን ሳያይ ችሎቱ ፋይሉን ዘግቶ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲዛወር ማድረጉ ከህገሪቱ ህግ ውጭ የተፈጸመ ውንብድና ነው ተብሎዋል፡፡

ሚያዝያ 25 እና 26 ቀን 2006 ዓ.ም ከስራ ገበታቸው እና ከየመኖሪያቸው ተይዘው ለእስር የተዳረጉት እነዚሁ ጋዜጠኞች እና ጦማርያን እንደ ከባድ ወንጀለኛ ተቆጥረው የዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች ጭምር ባሉበት እጃቸው በካቴና ታስሮ በአራዳ ምድብ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ለብዙ ግዜ ሲመላለሱ የቆዩ ቢሆንም ሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም ጠበቆች እና እስረኞቹ ባልተገኙበት በምስጢር ፋይሉ ተዘግቶዋል ተብሎ በመነገሩ ጠበቆቻቸውን ጭምር ግራ ያጋባ እንደሆነ ታውቆዋል፡፡

ሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም በአራዳ ምድብ 1ኛ ወንጀል ችሎት ቀጠሮ የነበራቸው በመሆኑ ጠበቆቻቸው በስፈራው ተገኝተው በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ እስረኞቹም ሳይመጡ ጠበቆቹንም ሳያነጋግሩ በቢሮ ውስጥ  ብቻ ፖሊስ ምርመራውን መጨረሱን በመግለፁ ፋይሉ እንዲዘጋ መደረጉ የህግ አግባብነትን ያልተከተለ ከባድ ውንብድና መሆኑን የህግ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

ፖሊስ ምርመራውን መጨረሱን ካስታወቀ የእስረኞቹ የዋስትና መብት ሊከበር ሲገባ አሊያም ክስ ተመስርቶባቸው በህጋዊ ሂደት ፍርዱን ማጠናቀቅ ሲገባ ጠበቆቻቸው በችሎት እየተጠባበቁ እያለ በምስጢር በቢሮ ውስጥ ፋይሉ ተዘግቶዋል ተብሎ ውሳኔ መተላለፉ  አሳፋሪና ፍጹም ከህግ ውጭ ነው  ተብሎዋል፡፡

ፋይሉ ከአራዳ ፍርድ ቤት ተዘግቶ ወደ ፌዴራሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውሮዋል ተብሎ ይነገር እንጂ ቀጠሮ መቼ እንደሆነ ለጠበቃውም ሆነ ለእስረኞቹ ያልተነገራቸው በመሆኑ ጋዜጠኞቹና

ቤተሰቦቻቸው ጭምር ግራ ተጋብተው እንደሚገኙ ታውቆዋል፡፡

ከሰኞ ሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ክፍሎች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ቢጠይቁም ምንም ምላሽ ያላገኙ ሲሆን ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ግዜ ድረስ ጋዜጠኞቹም ሆኑ ጦማርያኖቹ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያልተመሰረተባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡

በመጨረሻም ወያኔ በፖለቲካ አሳብቦ በዘጠኝ ጋዜጠኞች ላይ የመሰረተውን የፈጠራ ክስ ማቆም እንዳለበት ለጋዜጠኞች መብት መከበር የሚታገል ድርጅት ሲ.ፒ.ጄ የተባለው ዓለም አቀፍ ተቋዋም ጠየቀ፡፡

ለ80 ቀናት በማዕከላዊ እስር ቤት ያለ አንዳች ክስ ታስረው የከረሙት ጋዜጠኞቹ አንድም ክስ ሳይመሰረትባቸው ይልቁንም እንደ ከባድ ወንጀለኛ ለተቀረው ሕዝብ ማስፈራሪያ በሚል እጃቸው በካቴና ታስሮ እንዲሰቃዩ በመድረጋቸው የሰብአዊ መበት ጥሰት የተፈጸመባቸው መሆኑን በማውገዝ የተለጠፈባቸው የፈጠራ ክስ ተነስቶ ባስቸኳይ እንዲፈቱ ጠይቆዋል፡፡

በሌላ ዜና አንድ ስሙ ያልተጠቀሰ የጋምቤላ ተወላጅ የሆነ ኢትዮጵያዊ ከተሰደደበት ከኬኒያ የእንግሊዝ መንግስት ለወያኔ ድጋፍና እርዳታ በመስጠት ብዙ አርሶ አደሮች ከቦታቸው ላይ እንዲፈናቀሉና በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዲኖሩ በማድረግ ወንጀል ፈጽሟል በሚል በእንግሊዝ ፍርድ ቤት ላይ ክስ ለመመስረት ያቀረበውን ጥያቄ ክሱን እንዲመሰርት እርዳታ የተሰጠው መሆኑ ታውቋል። ከሳሹ አርሶ አደር የእንግሊዝ መንግስት 1.3 ቢሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ አምባገነነና ጨፍጫፊ ለሆነው የወያኔ ድርጅት እርዳታ በመስጠት በዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ደሃ አርሶ አደሮች ከቀያቸው እንዲፈናቀሉና በሚያሰቅቅ ድህነት ውስጥ እንዲኖሩ ተባብሯል የሚል ክስ አቅርቧል። የእንግሊዙ እርዳታ የደሃ አርሶ አደሮችን ችግር ከመቅረፍና ኑሯቸውን ከማሻሻል ይልቅ የእነዚህን አርሶ አደሮች የስቃይ ኑሮ ይበልጥ እንዲባባስ አድርጓል ብሏል። ይህ ክስ ለእንግሊዝ መንግስት አሳፋሪ ክስተት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ለአርሶ አደሩ የሚፈርድ ከሆነ የእንግሊዝ መንግስት የሚሰጠውን ለማስተካከል የሚገደድ መሆኑ ይገመታል።

ቤካ